**ኢትዮጵያ፤ ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ሪፖርት (2015)**

ኢትዮጵያ ለግዳጅ ሥራ እና ለወሲብ ንግድ ለሕገወጥ የሰዎች ዝውውር የተዳረጉ ወንዶች፣ ሴቶች እና ሕፃናት መነሻ፤ በተወሰነ ደረጃም መዳረሻ አገር ናት፡፡ ከኢትዮጵያ የገጠር አካባቢዎች የሚወጡ ወጣት ሴቶች፤ በአገሪቱ ውስጥ በቤት ሠራተኝነት እና፣ አልፎ አልፎም፣ በሴተኛ አዳሪነት ይበዘበዛሉ፤ ወጣት ወንዶች ደግሞ በባህላዊ ሽመና፣ በእረኝነት፣በጥበቃ እና በጎዳና ላይ ንግድ በግዳጅ እንዲሠሩ ይደረጋሉ፡፡ አዲስ አበባ የሚገኘው ዋና የገበያ ማዕከል ከአፍሪካ ቀዳሚው የወሲብ ንግድ ቤቶች መገኛ ሲሆን ዕድሜያቸው እስከ 8 ዓመት የሚሆኑ ልጃገረዶች በነዚህ ቤቶች በሴተኛ አዳሪነት ተሰማርተዋል፡፡ ኢትዮጵያውያን ወጣት ሴቶች ከኢትዮጵያ ውጪም በተለይ ጂቡቲ፣ደቡብ ሱዳን እና በመካከለኛው ምስራቅ አገራት ውስጥ በቤት ሠራተኝነት እና በሴተኛ አዳሪነት እንዲሰሩ ይገደዳሉ፤ ኢትዮጵያውያን ወጣት ወንዶች ደግሞ ጂቡቲ ውስጥ በሱቅ ሰራተኝነት፣ በተላላኪነት፣ በቤት ሰራተኝነት፣ በስርቆት እና የጎዳና ልመና ላይ እንዲሰሩ ይገደዳሉ፡፡ ወጣት ወንዶች  ከኢትዮጵያ ገጠር አካባቢዎች የተሻለ ሕይወት እንደሚገጥማቸው ቃል እየተገባላቸው በስፋት ይመለመላሉ፡፡ ለዚህም ምክንያቱ በመካከለኛው ምሥራቅ ርካሽ ጉልበት ስለሚፈለግ ነው፡፡

ባለሥልጣናት በህጋዊ መንገድ በቀን እስከ 1,500 የሚሆኑት እንደሚወጡ ሪፖርት አድርገዋል፡፡በርካታ ወጣቶች ሥራ ፍለጋ ወደ መካከለኛው ምሥራቅ ሲሰደዱ ጂቡቲ፣ ግብጽ፣ ሶማሊያ፣ ሱዳን እና ኬንያን እንደመሸጋገሪያ ይጠቀማሉ፡፡ ከነዚህ አንዳንዶቹ ሊሄዱ ካሰቡበት አገር ሳይደርሱ እንደመሸጋገሪያነት ባረፉበት አገር ተይዘው ለብዝበዛ፣ለእስራት፣ለግዳጅ ሥራ እና ለመታገት ይዳረጋሉ፡፡ በደቡብ ኢትዮጵያ አድርጎ ወደ ደቡብ አፍሪካ በርካታ ኢትዮጵያውያን እንደሚጓዙ፤እንዲሁም ቀይ ባህርን በጀልባ አቋርጠው የመን ሊገቡ ሲሉ በርካታ ኢትዮጵያውያን እንደሚሞቱ የሚጠቁሙ ሪፖርቶች ቁጥር እያደገ መጥቷል፡፡ ከነዚህ አብዛኛዎቹ በህገወጥ ስደት ወደነዚህ ማዳረሻዎች ሲያቀኑ ለህገወጥ ዝውውር ይዳረጋሉ፡፡ ወጣት ሴቶች በመካከለኛ ምሥራቅ ፣ በሱዳን እና ደቡብ ሱዳን ለቤት ሠራተኝነት ይዳረጋሉ፡፡ በመካከለኛው ምሥራቅ በቤት ሰራተኝነት የተሰማሩ በርካታ ኢትዮጵያውያን ሴቶች አካላዊ እና ወሲባዊ ጥቃት፣ ደሞዝ ክልከላ፣ የእንቅልፍ መነፈግ፣ የፓስፖርት መያዝ፣ በቤት ውስጥ መታገት እና ግድያን ጨምሮ አስከፊ ጥቃቶች ይደርሱባቸዋል፡፡ ኢትዮጵያውያን ሴቶች ሥራ ፍለጋ ሲሰደዱ ወይም በመካከለኛው ምሥራቅ ከሚበዘብዟቸው ቀጣሪዎች ለማምለጥ ሲሉ አንዳንዴ የህገወጥ የወሲብ ንግድ ሰለባ ይሆናሉ፡፡ በቂ የሙያ ክህሎት ሳይኖራቸው ወደ ሳዑዲ አረቢያ፣ የባህረ-ሰላጤው አገሮች እና ሌሎች የአፍሪካ አገሮች ከሚሰደዱ ኢትዮጵያውያን ወንዶች አንዳንዶቹ በእነዚህ አገራት ለግዳጅ የጉልበት ሥራ ይዳረጋሉ፡፡ በወረዳ ደረጃ ያሉ ባለሥልጣናት ጉቦ ተቀብለው በወረዳ በሚሰጡ የመታወቂያ ወረቀቶች ላይ የህፃናትን ዕድሜ እንደሚቀይሩ፤ህፃናት ያለወላጅ ፈቃድ ፓስፖርት እንዲወጣላቸውና ህገወጥ ሥራ ላይ ለመሰማራት ሀገር ለቀው እንዲወጡ እንደሚያደርጉ ሪፖርቶች አመልክተዋል፡፡

የኢትዮጵያ መንግሥት እ.ኤ.አ.  ከጥቅምት 2013 ጀምሮ በውጭ አገር የሥራ ቅጥር ላይ ክልከላ አድርጓል፡፡ ከ400 የሚበልጡ ኤጀንሲዎች ሰራተኞችን ወደ ውጭ አገራት የመላክ ፈቃድ ተሰጥቷቸው ነበር፤ ሆኖም መንግስት ከነዚህ ኤጀንሲዎች አብዛኞቹ ሕጋዊ እና ሕገወጥ የቅጥር ሂደቶችን እንደሚከተሉ በመገንዘቡ ለውጭ አገር በሚደረግ የሥራ ቅጥር ላይ ክልከላ ጥሏል፡፡ እ.ኤ.አ. ከህዳር እስከ መጋቢት 2014 የሳውዲ ዓረቢያ መንግሥት ቪዛና የቅጥር

ወረቀት የላቸውም በሚል ከ170,000 የሚበልጡ ኢትዮጵያውያንን ከሀገር አስወጥቷል። ዓለም አቀፍ ድርጅቶችም ሆኑ የኢትዮጵያ ባለሥልጣናት ከነዚህ በሺዎች የሚቆጠሩት የህገወጥ የሰዎች ዝውውር ተጠቂዎች እንደነበሩ ይገነዘባሉ። በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ የስደተኛ ካምፖችን እንደመሸጋገሪያነት የሚጠቀሙ የኤርትራ ስደተኞች በሱዳንና በግብጹ የሲናይ ባህረ-ሰላጤ የህገወጥ ዝውውር ችግሮች ያጋጥሟቸዋል። ከነዚህ አንዳንዶቹ በፈቃደኝነት ካምፖቹን ለቀው የሚሰደዱ ሲሆን፤የተቀሩት ተታለው ወይም ተጠልፈው ከካምፖቹ ይወሰዳሉ።

የኢትዮጵያ መንግሥት ሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውርን ለማስወገድ የተቀመጡትን ዝቅተኛ መስፈርቶች ሙሉ በሙሉ ባያሟላም፣ ችግሩን ለመቅረፍ ከፍተኛ ጥረት እያደረገ ይገኛል። መንግሥት ከሳውዲ ዓረቢያ ከስደት የተመለሱትን ዜጎች መልሶ ለማቋቋም መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶችና ከዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር ተቀራርቦ በመሥራት የሥራ ዕድሎችን በማመቻቸት ዙሪያ ሠርቷል። የዜጎች ከሌሎች ሀገራት መባረርና የብዙ ኢትዮጵያውያን በውጭ ሀገራት ሥራ ማግኘት ፍላጎት ካሳደረው የረጅም ጊዜ ተጽዕኖ አኳያ፤መንግሥት በማህበረሰብ-አቀፍ ውይይት ፕሮጀክት አማካይነት እስከታችኛው መዋቅር ድረስ ወርዶ ህገወጥ የሰዎች ዝውውርንና ተያያዥ ወንጀሎችን የመከላከልና የኅብረተሰቡን ግንዛቤ የማሳደግ ጥረቱን አጠናክሮ ቀጥሏል። በተጨማሪም መንግሥት ከስደት የተመለሱ ዜጎችን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፍላጎቶች በማጥናት በመልሶ ማቋቋም ለሚደረገው ጥረት አጋዥ ይሆን ዘንድ የሥራ ዕድሎችን ፈጥሯል። በዓመቱ ውስጥ መንግሥት በውጭ ሀገራት የሥራ ስምሪት ላይ በጊዜያዊነት የጣለውን እገዳ እንደሚያነሳ፤ አገናኝ ኤጀንሲዎችን በተሻለ መልኩ እንደሚቆጣጠርና በውጭ ሀገራት ተቀጥረው የሚሠሩ ዜጎቹን ደህንነት እንደሚጠብቅ በይፋ ቢገልጽም እገዳውም አልተነሳም፤የተባለው ጥበቃም ለጊዜው ተግባራዊ አልሆነም። ለአገር ውስጥም ሆነ ለድንበር ተሻጋሪ የሕገወጥ ዝውውር ሰለባዎች የገንዘብም ሆነ የቁሳቁስ ድጋፍ የሚያደርጉት መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሲሆኑ ለነዚህ ድርጅቶች የገንዘብም ሆነ የቁሳቁስ እርዳታ አላደረገም። ህግ አስፈጻሚ አካላት የሚደርጉት ጥረት በመጠኑም ቢሆን መቀነሱ ተስተውሏል፤ መንግሥት እ.ኤ.አ. በ2014 የህገወጥ ዝውውር ሰለባዎችን በመለየት ሥራ ስንት ተጠቂዎች እንደተገኙ አልገለጸም፤ ተጠቂዎችን ለመለየት የተገኙትን መረጃዎች ለማጋራት መንግሥት መደበኛ የሆነ ሥርዓት አልዘረጋም። በተጨማሪም መንግስት የሕጻናት የወሲብ ንግድን እና ሌሎች በአገር ውስጥ የሚፈጸሙ ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ወንጀሎችን በሕግ ማስከበር፣ ከለላ በመስጠት እና በመከላከል በኩል በቂ ሥራ አልሠራም።



## በኢትዮጵያ ህገወጥ የሰዎች ዝውውርን ለማስቆም የሚረዱ የመፍትሄ ሐሳቦች

ሕገወጥ ቅጥር ፈጻሚዎችን መቅጣት በሚቻልበት መልኩ የሥራ ቅጥር አዋጁን ማሻሻል እንዲሁም በውጭ አገራት ሥራ የሚያስቀጥሩ ኤጀንሲዎች ላይ የሚደረገውን ቁጥጥር ማጥበቅ፤የቅጥር ውሎችን የሚያፀድቁ ኃላፊዎችን ግንዛቤ ለማሳደግ መደበኛ የሆነ የግንዛቤ ማስጨበጫ የሥልጠና ሥርዓት መዘርጋት ወይም ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎችን መቆጣጣር፤በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ለተዘረዘሩ ለወሲብ ንግድና ህገወጥ የሰዎች ዝውውር ወንጀሎች የተቀመጡትን ቅጣቶች ማክበድ፣ የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ አንቀጽ 597 እና 635ን ሕገወጥ የሰዎች ዝውውርን ግልፅ ትርጉም ባካተተና ወንድ የህገወጥ የሰዎች ዝውውር ሰለባዎች ራሱን በቻለ አንቀጽ በሕጉ እንዲሸፈኑ በሚያደርግ መልኩ ማሻሻል፣ እንዲሁም ቅጣቶችን በሌሎች ከባድ ወንጀሎች ላይ ከሚጣሉ ቅጣቶች ጋር እንዲጣጣሙ በሚያደርግ መልኩ ማሻሻል፤ በመላ ሀገሪቱ የፖሊስን የወንጀል ምርመራ አቅም ማጎልበት በአገር ውስጥ የሚፈፀመውን ህገወጥ የሕጻናት ዝውውር ወንጀል ፈጻሚዎችን (ባለስልጣናትን ጭምር) ለሕግ ማቅረብ፤በጉልበት ብዝበዛ እና በወሲብ ንግድ ዓላማ የሚካሄዱ የሰዎች ዝውውር ወንጀሎችን ለመቅጣት የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉን አንቀጾች 596፣597 እና 635 ይበልጥ በተግባር ላይ ማዋል፣ ብሔራዊ መታወቂያዎች እና ፓስፖርቶች በሚሰጡበት ወቅት የሚከናወነውን የማጣራት ሥራ በማሻሻል ሕጻናት አጭበርብረው እነዚህን ሰነዶች እንዳላገኙ ማረጋገጥ፤ በመንግሥትም ሆነ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የሚተዳደሩ የሰለባዎች መጠለያዎች ያልተቋረጠ አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ በጀት መመደብን ጨምሮ ከስደት ለሚመለሱ የሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ሰለባዎች የሚሰጡ አገልግሎቶችን ደረጃ ለማሳደግ ከአገር በቀል መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር ተባብሮ መሥራት፤ ፤ በኢትዮጵያ ኤምባሲዎች ውስጥ የሠራተኞች ጉዳይ አታሼዎችን መመደብ እንዲቻል አስፈላጊውን በጀት መያዝ፤ በውጭ አገራት ለሚሾሙ ዲፕሎማቶች እና የሥራ ቅጥር ውሎችን ሕጋዊነት ለሚያረጋግጡ የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ የሥራ ኃላፊዎች ስለ ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ግንዛቤ የሚያስጨብጡ መደበኛ ሥልጠናዎች በመስጠት በውጭ አገራት ተቀጥረው ለመስራት ለሚፈልጉ ኢትዮጵያውያን ከለላ መስጠት፤ ወደ መካከለኛው ምሥራቅ እና ሌሎች አገራት ለሚጓዙ ስደተኛ ሠራተኞች በሚሰጠው የቅድመ ጉዞ ሥልጠና ውስጥ ሕገወጥ የሰዎች ዝውውርን እና የሠራተኛ መብትን የሚመለከት መረጃ ማካተት።

## በህገወጥ የሰዎች ዝውውር ወንጀል ፈጻሚዎችን ለህግ የማቅረብ ሂደት

የኢትዮጵያ መንግሥት ህገወጥ የሰዎች ዝውውርን ለመቆጣጠር ያወጣውን ሕግ በሥራ ላይ ለማዋል ጥረት ማድረጉን እንደቀጠለ ነበር። ሆኖም ይህ ጥረት ሙሉ በሙሉ ያተኮረው በድንበር ተሻጋሪ የሰዎች ዝውውር ላይ ሲሆን፤ለወሲብ ንግድ ዓላማ ወይም በአገር ውስጥ የሚደረጉ ለግዳጅ ስራ የታለሙ ሕገወጥ ዝውውሮች ላይ መንግስት ምርመራ ማድረጉን ወይም ክስ መመስረቱን የሚያሳዩ ማስረጃዎች ጥቂት ናቸው። የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀፅ 596 (ለባርነት መዳረግ)፣አንቀፅ 597 (ሕገወጥ የሴቶች እና የሕጻናት ዝውውር)፣አንቀጽ 635 (የሴቶች እና የሕፃናት ዝውውር) እንዲሁም አንቀጽ 636 (የወንጀል ማክበጃ ሁኔታዎች) ለወሲብ ንግድ ዓላማ ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር መፈጸም የተከለከለ ተግባር እንደሆነ ይደነግጋል። ለወሲብ ንግድ  የሰዎች ዝውውር መፈጸምን የሚከለክለው አንቀጽ 635 ከአምስት

ዓመት ያልበለጠ የእሥር ቅጣት ይጥላል፤ይህ በራሱ ከባድ ሊባል የሚችል ቢሆንም፣ አስገድዶ መድፈርን ለመሳሰሉ ሌሎች ከባድ ወንጀሎች ከተቀመጡ ቅጣቶች ጋር ሲነፃፀር ግን አነስተኛ ነው። አንቀጽ 596 እና 597 ባርያ አሳዳሪነት እና የጉልበት ብዝበዛ ዓላማ ያለው የሰዎች ዝውውር ሕገወጥ ተግባራት እንደሆኑ የሚደነግጉ ሲሆን፤ ለነዚህም ከአምስት እስከ ሃያ ዓመታት የሚደርስ ከባድ የእስር ቅጣት ይጥላሉ። ነገር ግን አንቀጽ 597 እና 635 ለሕገወጥ የሰዎች ዝውውር የጠራ ትርጉም ካለመስጠታቸውም ሌላ፤ በአዋቂ ወንዶች ላይ ለሚፈጸሙ ወንጀሎች የሚጣል ቅጣትን አያካትትም። በመሆኑም ከሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ጋር የሚያያዙ ጥፋቶችን ተከትሎ ክስ ለመመስረት እምብዛም ጥቅም ላይ አይውሉም። መንግሥት በህገወጥ ዝውውር የተጠረጠሩ ሰዎችን ጉዳይ ለመመልከት የሚያስችል መረጃ በአንቀጾቹ ላይ አያቀርብም። ይሁንና አንድ ሀገር በቀል መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት በአንቀጽ 597 መሠረት በ9 ግለሰቦች ላይ ፍርድ ሊያስፈርድ መቻሉን ይህ ሪፖርት በሚጠናቀርበት ወቅት አመልክቷል። በአጠቃላይ በጉልበት ብዝበዛ ዓላማ የሚፈፀሙ ድንበር ተሻጋሪ የሰዎች ዝውውር ወንጀሎችን የሚመለከቱ ጉዳዮችን ለመዳኘት አዘውትረው ጥቅም ላይ የሚውሉት አንቀጽ 598 (ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ ኢትዮጵያውያንን ወደ ውጭ አገር ስለ መላክ) እና አንቀፅ 571 (የሌላ ሰውን ሕይወት አደጋ ላይ መጣል) ናቸው። ለሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ግልጽና ሕጋዊ ትርጓሜ ባለመኖሩ መንግሥት እንዲህ ዓይነት ጉዳዮችን የመመርመር እና ለፍርድ የማቅረብ አቅሙ ተገድቧል። ባለሥልጣናት የሥራ ስምሪት አዋጅ ቁጥር 632/2009 ላይ ማሻሻያ ለማድረግ የሚያስችሉ ረቂቆችን ማዘጋጀት ቀጥለዋል።

በፌደራል ፖሊስ የተደራጀ ወንጀል ምርመራ ዩኒት ሥር ያለው ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር እና የአደንዛዥ ዕጽ ዝውውር መቆጣጠሪያ ክፍል ሪፖርቱ በሚሸፍነው የጊዜ ገደብ ውስጥ በ99 መዝገቦች ላይ ምርመራ አድርጓል። በቀደመው ዓመት ይህ አኃዝ እ.ኤ.አ. በ2013 135 ነበር። የፌዴራል መንግሥት ከድንበር ተሻጋሪ ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ጋር በተያያዘ 118 ተከሳሾች የተካተቱበት 93 መዝገቦችን መመርመሩን ሲገልፅ፤ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከነዚህ መካከል በ46ቶቹ ላይ ፍርድ ማሳለፉን አስታውቋል። ባለፈው ዓመት 106 በሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ላይ የተሰማሩ ግለሰቦች ፍርድ ተሰጥቷል። ባለሥልጣናት 58 ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮች በመታየት ላይ መሆናቸውን አመልክተዋል። የመንግሥት ባለሥልጣናት በክሶቹ ላይ ዝርዝር መረጃም ሆነ በአጥፊዎቹ ላይ በአማካይ ምን ያህል ቅጣት እንደሚጣል ወጥ የሆነ መረጃ አያቀርቡም። አልፎ አልፎ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በሚያቀርቧቸው ሪፖርቶች መሠረት ከሁለት እስከ 11 ዓመት የእስር ቅጣት እንደሚጣል ተጠቁሟል። እ.ኤ.አ. በደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ሥር የሚገኙ የወረዳ ፍርድ ቤቶች በህጻናት ሕገወጥ አዘዋዋሪነት የተጠረጠሩ ግለሰቦችን ያካተቱ 468 ጉዳዮችን እንደተመለከቱ ሪፖርት ተደርጓል። ይሁንና ስንቶቹ ለፍርድ እንደቀረቡ ወይም ፍርድ እንደተሰጣቸው የሚያመለክት በቂ መረጃ ከሪፖርቱ ጋር አልቀረበም። እ.ኤ.አ. መጋቢት 2015 መንግሥት 38,000 ሰዎችን በህገወጥ መንገድ ወደ ደቡብ አፍሪካ እና ወደ መካከለኛው ምሥራቅ በማጋዝ የህገወጥ ዝውውር ሰለባ ያደረጉ የሁለት ግለሰቦችን ጉዳይ በማጣራት ላይ ይገኛል።

መንግሥት እ.ኤ.አ. በ2014 ሕጻናትን በወሲብ ንግድ ላይ እንዲሰማሩ የሚስገድዱ አዘዋዋሪዎችን ጨምሮ ሰዎችን ለወሲብ ንግድ በሚያዘዋውሩ ተጠርጣሪዎች ላይ ክስ አልመሠረተም። በአገር ውስጥ የሚፈጸሙ የሰዎች ማዘዋወር ወንጀሎችን በመመርመርና ለሕግ በማቅረብ ወይም ክልላዊ

መንግሥታት ይህን እንዲያደርጉ በማብቃት በኩል መንግሥት በቂ ጥረት አላደረገም። የክልል ሕግ አስከባሪ አካላት የሕገወጥ የሰዎች ዝውውርን የተመለከተ ሥልጠና ቢወስዱም፤ ጉዳዮችን በአግባቡ የመመርመር ብሎም ተያያዥ መረጃዎችን የመሰብሰብ እና የማደራጀት አቅም ውሱን ነበር። በዓመቱ ውስጥ የመንግሥት ባለሥልጣናት ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ፖሊስ እና ሌሎች በኃላፊነት ደረጃ ያሉትን አካላት አሠልጥነዋል። በአጠቃላይ 456 የፖሊስ መኮንኖች፣ 115 የሥራና ሠራተኛ ጉዳይ መርማሪዎች፣ 139 ዳኞች እና ሌሎችም አካላት በህጻናት ጉልበት ብዝበዛ እና ህገወጥ የሰዎች ዝውውርን በመለየት፣በመመርመርና ሪፖርት በማድረግ ዙሪያ ሥልጠና ወስደዋል። መንግሥት ከሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ወንጀል ፈፃሚዎች ጋር ተባብረዋል በተባሉ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች ላይ ምርመራ ማድረጉን፣ ክስ መመስረቱንም ሆነ ማስቀጣቱን  በሚመለከት ምንም ሪፖርት አላቀረበም። በወረዳ ደረጃ ያሉ ኃላፊዎች ጉቦ በመቀበል በመታወቂያ ካርዶች ላይ የዕድሜ ለውጥ እንደሚያደርጉ፤ ፓስፖርት የሚሰጡ መስሪያ ቤቶች ደግሞ የመታወቂያውን ትክክለኛነትም ሆነ የአመልካቾቹን ዕድሜ ስለማያጣሩ ሕጻናት ያለወላጆች ስምምነት ፓስፖርት እንደሚያወጡ ሪፖርቶች ያመለክታሉ።

## ለህገወጥ ዝውውር ሰለባዎች የተሰጠ ከለላ (ጥበቃ)

መንግሥት ለሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ሰለባዎች በቂ እገዛ አላደረገም። በዚህ ረገድ መንግሥት ሙሉ ለሙሉ ሊባል በሚችል መልኩ ለህገወጥ ዝውውር ሰለባዎች የሚያስፈልገውን አገልግሎት ለዓለም አቀፍ ድርጅቶች እና መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች የሰጠ ሲሆን፤ ለነዚህ ድርጅቶች ምንም ዓይነት የገንዘብ ድጋፍም አላደረገም። ነገር ግን እ.ኤ.አ. በ2013 የሳዑዲ ዓረቢያ መንግሥት በርካታ ኢትዮጵያውያን ስደተኛ ሠራተኞችን ከአገሩ ማስወጣቱን ተከትሎ መንግሥት 170,000 የሚሆኑ ከስደት ተመላሾችን መልሶ ማቋቋሙን ቀጥሏል። ሕገወጥ የሰዎች ዝውውርን የሚከላከለው ግብረኃይል ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ከስደት የተመለሱ ኢትዮጵያውያን ምን አይነት ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች እንዳሉባቸው ዘርዘር ያለ ትንታኔ አቅርበዋል። የገቢ ማስገኛ መንገዶችንና የመልሶ ማቋቋሚያ ዕቅድ ያቀረቡ ቢሆንም፤ዕቅዱ መቼ ተግባራዊ እንደሚሆን ግልፅ የሆነ ነገር አልተቀመጠም። ሰማኒያ አንድ በመቶ የሚሆኑት ከስደት ተመላሾች ሥራ ፈጠራና ሥነልቦናዊ እገዛን ጨምሮ መንግሥትን እንደዋንኛ የድጋፍ ምንጭ የጠቀሱ ቢሆንም፤ ሌሎች በርካታ ከስደት ተመላሾች መንግሥት በጥቃቅንና አነስተኛ መስኮች እንዲሰማሩ፣ እንዲሁም ለእርሻ የሚሆን መሬት ማግኘት እንዲችሉ ለማድረግ በቂ በጀት ባለመመደቡና ያለው አቅም ዝቅተኛ መሆኑን አመልክተው በዚህም ደስተኛ አለመሆናቸውን ገልጸዋል።

መንግሥት በዓመቱ የህገወጥ የሰዎች ዝውውር ሰለባዎችን በመለየት ምን ያህል ድጋፍ እንዳደረገላቸው ሪፖርት አላቀረበም። አስቸኳይ ምላሽ የሚሰጡ አካላት የሚጠቀሙበትንም ወጥ የአሠራር መመሪያዎችን ሳያዘጋጅ በመቅረቱ እነዚህ አካላት የህገወጥ የሰዎች ዝውውር ሰለባዎችን የመለየትና ለእርዳታ ጥቆማ መስጠት ሥራ በሚሠሩበት ወቅት እንቅፋት ፈጥሮባቸዋል። አብዛኛው ዕርዳታ ድንበር አቋርጠው ለመጡ ተመላሾች ምግብና ውሃ፣ህክምና፣ጊዜያዊ መጠለያና ወደመጡባቸው አካባቢዎች የሚያደርስ የትራንስፖርት አገልግሎትን ጨምሮ በጊዜያዊ ፍላጎቶች ላይ ያተኮረ ነው። መንግሥት በአፋር ክልል ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር በመተባበር የአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ መስጠቱን ቀጥሏል። በአዲስ አበባ ያለ አንድ ድርጅት ከ400 ለሚበልጡ ከሳውዲ ተመላሾች የሥነልቦናና የመልሶ ማቋቋም ድጋፍ ሲሰጥ፤ሌላ አንድ መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ቁጥራቸው ቢያንስ 85 ለሚሆን ህጻናት የህገወጥ ዝውውር ሰለባዎች እገዛ ማድረጉን ሪፖርት አድርጓል። ይሁንና እነዚህ ድርጅቶች ላደረጉት

ጥረት መንግሥት ምንም ዓይነት ድጋፍ አላደረገላቸውም። የተለያዩ የወረዳ የሴቶችና የወጣቶች መምሪያዎች ለበርካታ የህገወጥ የህጻናት ጉልበት ብዝበዛ ሰለባዎች ሥነልቦናዊና ማህበራዊ ድጋፍ በመስጠት ህጻናቱ ከቤተሰቦቻቸው ጋር እስኪቀላቀሉ ድረስ ለአደጋ በማያጋልጡ ጊዜያዊ ማዕከላት እንዲቆዩ አድርገዋል።አብዛኛዎቹ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የሚመሩ የድጋፍ ተቋማት ደግሞ ፕሮጀክትን መሠረት ባደረገ የገንዘብ ድጋፍ ላይ ጥገኛ በመሆናቸው በዘላቂነት አገልግሎት ሊሰጡ አይችሉም። ለሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ሰለባዎች ክብካቤ የማድረግን ጉዳይ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ትከሻ ላይ የጣለው መንግሥት እ.ኤ.አ. በ2009 ባወጣው የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት አዋጅ አማካይነት በነዚሁ ድርጅቶች ላይ ችግር ፈጥሯል። አዋጁ ከገቢያቸው 10 በመቶ በላይ ከውጭ ምንጮች የሚያገኙ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች በሰብዓዊ መብት፣ በሕጻናት መብቶች፣ በአካል ጉዳተኞች መብቶች እና በፍትህ ላይ እንዳይሰማሩ ይከለክላል። እነዚህ ክልከላዎች አንዳንድ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ሰለባዎች በአዘዋዋሪዎቻቸው ላይ ክስ እንዲመሰርቱ እና ቤተሰቦቻቸውን ፈልገው እንዲያገኙ ማገዝን የመሳሰሉ የተሟላ የከለላ አገልግሎት እንዳይሰጡ አሉታዊ ተጽዕኖ ፈጥረውባቸዋል።

መንግሥት በአዲስ አበባ በአስሩም ክፍለ ከተሞች እና በስድስት ታላላቅ ከተሞች ለሕጻናት ከለላ የሚሰጡ ማዕከላት አቋቁሟል። በነዚህ ማዕከላት የሚያገለግሉ ሠራተኞች ሕገወጥ የሕጻናት ዘውውርን ጨምሮ ለአደጋ ተጋላጭ ለሆኑ ሕጻናት ክብካቤ በማድረግ የሠለጠኑ ናቸው። ባለሥልጣናት ተጎጂዎች ጉዳት ያደረሱባቸው አካላት ጥቆማ በማድረግ እንዲመረመሩና ለፍርድ እንዲቀርቡ ትብብራቸውን ቢጠየቁም ተጎጂዎች በሂደቱ ላይ በበቂ ሁኔታ እንዳይሳተፉ ምንም ዓይነት የከለላ ሥርዓት አለመዘርጋቱ አግዷቸዋል። የኢትዮጵያ ህግ የውጭ ሀገራት ተጠቂዎች አደጋ ወዳሉባቸው መዳረሻዎች እንዳይወሰዱ አይከለክልም። እ.ኤ.አ. በ2014 ስለ ህገወጥ ዝውውር ሰለባዎች መያዝ፣መታሰርና ለፍርድ መቅረብ የሚገልጽ ሪፖርት አልቀረበም። በውጭ ሀገራት ላሉ ኢትዮጵያዊ ሠራተኞች የሚሰጠው አገልግሎት ውስን ሆኖ በመቀጠሉ የመንግሥት ዕርዳታ ደካማ ነበር። አሁን ያለው የሥራና ሠራተኛ አገናኝ አዋጅ አገናኝ ኤጀንሲዎች የሠራተኛ የሥራ ውል በተቋረጠ ጊዜ የሚያገለግል ተቀማጭ ገንዘብ እንዲያስይዙ ይደነግጋል። ነገር ግን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ይህን ገንዘብ በመጠቀም ተጎጂዎችን ወደመንደራቸው አላጓጓዘም።

## ህገወጥ የሰዎች ዝውውርን ለመከላከል የተደረገ ጥረት

መንግሥት ሕገወጥ የሰዎች ዝውውርን ለመከላከል በሚያደርገው ጥረት ጥሩ እመርታ አሳይቷል። በተለይም በክልሎችና በብሔራዊ ደረጃ በህገወጥ የሰዎች ዝውውር መከላከያ ግብረኃይል የተከናወኑ የግንዛቤ መፍጠሪያ ዘመቻዎችን አስተባብሯል። ከሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችና ከኤጀንሲዎች ከተውጣጣው ብሔራዊ ግብረኃይል በተጨማሪም እያንዳንዱ ክልል በየሩብ ዓመቱ ስብሰባ የሚያካሂድ የራሱ የቴክኒክ ኮሚቴ አቋቁሟል። እ.ኤ.አ. በ2014 ብሔራዊ ግብረኃይሉ ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር በመተባበር በህገወጥ ሰዎች ዝውውር ላይ ያተኮረ የማህበረሰብ ውይይት ፕሮግራም አካሂዷል። በነዚህ ውይይቶች የወረዳና የቀበሌ ባለሥልጣናትን ጨምሮ በተመረጡ 325 አካባቢዎች ከ25 እስከ 40 ግለሰቦች ተሳትፈዋል። ብሔራዊ ግብረኃይሉ በሀገሪቱ የበርካታ የችግሩ ተጠቂዎች ወደሆኑ አራት ዋና ዋና ክልሎች

በሁለት ዙር የክትትልና የቁጥጥር ጉዞዎችን አድርጓል፡፡ የመንግሥት የሚዲያ ተቋማት በግብርናው ዘርፍ የህጻናት ጉልበት ብዝበዛ ላይ ያተኮሩ የፍርድ ቤት ተከታታይ ድራማዎችን አስተላልፈዋል፡፡

መንግሥት መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመተባበር 42,000 የሚሆኑ በህጻናት ጉልበት ብዝበዛ ዙሪያ መረጃ የሚሰጡ በራሪ ወረቀቶችንና የ6,500 ተጎጂዎችን ታሪክ የያዙ ጽሁፎችን አሰራጭቷል፡፡ በሌላም በኩል መንግሥት የህጻናት ጉልበት ብዝበዛና ህገወጥ የሰዎች ዝውውር በሚያስከትሏቸው ጉዳቶች ዙሪያ በተሠሩ ዘጋቢ ፊልሞችና የራዲዮ ፕሮግራሞች ላይ ተሳትፏል፡፡

መንግሥት ፈቃድ የሰጣቸው የሥራ ቅጥር ኤጀንሲዎች ሕጋዊና ሕገወጥ የሠራተኞች ስደት እንደሚያከናውኑ ስለደረሰባቸው እ.ኤ.አ ከጥቅምት 2013 ጀምሮ በአነስተኛ ሥራ ዘርፍ ለመሰማራት ወደውጭ በሚደረግ ሕጋዊ ጉዞ ላይ መንግሥት እገዳ ጥሏል፡፡ በሥራ ቅጥር ልውውጥ አዋጁ ላይ የግል የቅጥር አጀንሲዎችን ይበልጥ ለመቆጣጠር፣ በኢትዮጵያ ኤምባሲዎች ውስጥ የሠራተኞች ጉዳይ አታሼ ለመመደብ፤ እንዲሁም ስደተኛ ሠራተኞችን የመለየት እና የማሠልጠን ሥራ የሚያከናውን ገለልተኛ ኤጀንሲ ለማቋቋም የሚደረጉት ማሻሻያዎች እስከሚጸድቁ ድረስ እገዳው ይቀጥላል፡፡ መንግሥት የሥራ ቅጥር ኤጀንሲዎችን እንቅስቃሴ ተከታትሎ ስደተኞችን ወደአደገኛ ቦታዎች ልከዋቸዋል በሚል ቁጥራቸው ያልታወቀ አጀንሲዎች እንዲዘጉ አድርጓል፡፡ ሪፖርቱ በሚሸፍነው ክፍለ ጊዜ መንግሥት የተጣለውን እገዳ ተላልፈዋል በሚል ከ10 አገናኝ ኤጄንሲዎች የሥራ ፈቃድ ሰርዟል፡፡ባለስልጣናት የተጣለው የጉዞ እገዳ ሕገወጥ ስደትን ሊያበረታታ እንደሚችል በመገንዘባቸው፤ ከፌዴራል ፖሊስ ተጨማሪ በጀትና የሰው ኃይል መድበው በኢትዮጵያ ድንበሮች ላይ የሚደረገው ጥበቃ እንዲጠናከር አድርገዋል፡፡ መንግሥት ከጅቡቲ፣ ሱዳን፣ከዮርዳኖስ፣ከኩዌት፣ከየመንና ከኳታር መንግሥታት ጋር የተባበሩት ዓረብ ኤሚሬቶች እና ኬንያ መንግሥታት ጋር የሠራተኞች ስደት ስምምነቶችን የተፈራረመ ሲሆን፤ከሳውዲ ዓረቢያ፣ከሊባኖስ፣ከደቡብ ሱዳንና ከተባበሩት ዓረብ ኢሚሬቶች ጋር በድርድር ላይ ይገኛል፡፡ ከአፍሪካ ሀገራት ጋር የሚደረሱ ስምምነቶች የጋራ ድንበር ቁጥጥርን፤እንዲሁም የህገወጥ የሰዎች ዝውውር ሰለባዎችን መርዳትና ወደ ሀገራቸው መመለስን የሚያካትቱ ናቸው፡፡ ይሁንና ስምምነቶቹ የሠራተኛ መብቶችን በግልጽ አያስቀምጡም፡፡ በአጠቃላይ በአብዛኛው በመካከለኛው ምሥራቅ ከሚገኙ መዳረሻ ሀገራት ጋር የሚፈረሙ ስምምነቶች ትክክለኛ የሠራተኛ ምልመላን፣ህግ በሚጥሱ አካላት ላይ እርምጃ መውሰድን፣ለኢትዮጵያዊ ሠራተኞች እኩል ጥበቃ ማድረግን፣እንዲሁም ለተመሳሳይ ሥራ ተመሳሳይ ክፍያ መክፈልን፣ተቀባይነት ባለው የሥራ ሰዓትን መሠረት ያደረገ የአሠራር ሥርዓትንና አግባብነት ያለው የፈቃድ አሰጣጥ ሂደትን ለማረጋገጥ መንግሥታት ቁርጠኛ አቋም ሊይዙ ይገባል፡፡

እ.ኤ.አ. በ2012 መንግሥት በመላ አገሪቱ ያወጣውን የልደት ምዝገባ አዋጅ ለመተግበር ዕቅድ ይዞ ነበር፡፡ ሆኖም ወጥነት ያለው ብሔራዊ የመታወቂያ ካርድ ባለመኖሩ ይህ አዋጅ ሊተገበር አልቻለም፡፡ የመታወቂያ ካርዶችን በወረዳ ደረጃ መስጠት መቀጠሉ የተጭበረበሩ መታወቂያዎች እንዲዘጋጁ መንገድ ፈጥሯል፡፡ በዓመቱ መንግሥት የወሲብ ንግድን ወይም የግዳጅ ሥራን ለመቀነስ ምንም ዓይነት ጥረት አላደረገም፡፡ መንግሥት የህገወጥ የሰዎች ዝውውር ጉዳይን ለዲፕሎማቲክ ሠራተኞቹ የሚሰጠው መሠረታዊ ሥልጠና አካል በማድረግ ሠራተኞቹ ሥልጠናውን እንዲወስዱ አድርጓል፡፡ መንግሥት የአገር መከላከያ ሰራዊት አባላት ለዓለምአቀፍ

የሰላም ማስከበር ተልዕኮ ወደ ውጭ አገራት ከመሰማራታቸው በፊት የፀረ-ሕገ ወጥ ዝውውር ስልጠና የሰጠ ሲሆን፤ ስልጠናው የተሠጠው ከውጭ አገር በተገኘ ዕርዳታ ነው።